# የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግስት በክልሉ ቦታ ለማግኘት ለጠየቁ አመልካቾች ያወጣው

# ማስታወቂያ

የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግስት የዲያስፖራ ጉዳይና የህዝብ ግንኙነት ጽ/ቤት ከሐምሌ ወር መጀመሪያ ጀምሮ በአዋሣ ከተማ ለመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ ጥያቄ ከውጭ ሀገር የሚመጡ ኢትዮጵያውያንንና ትውልደ-ኢትዮጵያውያንን እየተቀበለ ሲመዘግብ ቆይቷል፡፡

የሁሉም አመልካቾች ጥያቄ በአዋሣ ከተማ ብቻ በመሆኑና አዋሣ ባለው ዝግጅት ሁሉንም አመልካቾች ማስተናገድ ባለመቻሉ ከሐምሌ ወር ጀምሮ እስከ ጳጉሜን 5 ቀን 1999 ዓ.ም. ብቻ የተመዘገቡ የመጀመሪያ 779 አመልካቾች ዝርዝር ለከተማ አስተዳደሩ ተላልፎ 3 አመትና ከዚያ በላይ መቆየታቸው እየተረጋገጠ ቦታ በመሰጠት ላይ ይገኛል፡፡

በአሁኑ ወቅት የአመልካቹ ቁጥር 2119 የደረሰ በመሆኑ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ <u>የአዋሣ ከተማ የመኖሪያ ቤት ጥያቄ ምዝገባ የቆመ መሆኑ ታውቆ</u> ከዚህ ቀጥሎ በቀረበው ዝርዝር ለተጠቀሱት ከተሞች ብቻ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ብቻ ተቀብለን የምናስተናግድ መሆኑን እየገለጽን ከመዝገብ ቁጥር 864 ጀምሮ ያላችሁ አመልካቾች በሁለተኛ የከተማ ምርጫችሁ መሠረት የተዘጋጀውን ደብዳቤ ከጽ/ቤታችን በመውሰድ ለመረጣችሁት ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት በማቅረብ ጉዳዩን እንድትከታተሉት እናሳስባለን፡፡

**ከሰላምታ ጋር**

የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች
ክልል መንግስት የዲያስፖራ ጉዳይና የህዝብ ግንኙነት ጽ/ቤት

## መሪ ከተማ (1ኛ ደረጃ)

አዋሳ *ምዝገባው የተጠናቀቀ*

## ከፍተኛ ከተማ (2ኛ ደረጃ)

አ/ምንጭ
ሶዶ
ዲላ
ሆሳዕና

## መካከለኛ ከተማ (3ኛ ደረጃ)

ይረጋዓለም
ቡታጅራ
ወልቂጤ
ሚዛን/አማን
ቴፒ

## ታዳጊ ከተማ (ሌሎች)

ቦንጋ
ዱራሜ
ወራቤ
ተርጫ
ማሻ
አረካ
ይ/ጨፌ
አለታ ወንዶ
ቦዲቲ
አላባ
ሳውላ
ጂንካ